**Sochii Dargaggoota Biyyoolessaa, Bilisummaa fi Dimokraasiif(SDBBD)**

**National Youth Movement for Freedom and Democracy (NYMFD)**

## *በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በሚኙ የኦሮሞ ልጆች ላይ የተላለፈ ኢፍትሀዊ ወሳኔ እና በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተከፈተው ዘመቻ ትግሉን ከግብ እንዳይደርስ አያደርገውም፤*

### *የወጣቱ(ቄሮ) የነፃነት ማለሻ*

እ.ኤ.አ ነሐሴ/2013 የወያኔው ፍርድ ቤት ባዋለው ችሎት በእነ ደቻሳ ዊርቱ ማዝገብ በተከሰሱ 24 የኦሮሞ ተማሪዎች ላይ ያስተላለፈው ወሳኔ ከእውነት የራቀና ሆን ተብሎ በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተከፈተው ዘመቻ አካል ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ ኢፍትሀዊ ወሳኔ የወያኔ መንግስት እና ቅጥረኞቹ በኦሮሞ ህዝብ ላይ እያደረሱ ለሚኙት ወደር የሌለው ግፍ እና በደል ከተጠያቂነት አያሚልጡም፡፡

የወያኔ መንግስት የኦሮሞ ተማሪዎችን ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በማብሰብ *"የኢፌዴሪ መንግስት በአግባቡ እና በፍትሀዊነት የኦሮሞን ህዝብ እያገለገለ አይደለም እያላችሁ ህዝቡ በመንግስት ላይ እንዲያምፁ ለሚድርግ አስተባብራችኋል ስለዚህ በአሸባሪነት ወንጀል ተጠያቂ ናችሁ"* በሚል የከሰሳቸው ሲሆን ችሎት በሚቋቋም በኦሮሞ ልጆች ላይ የረዥም እና የአጭር ጊዜ እስራት ብይን አስተላልፎባቸዋል፡፡ የመቡት ጥያቄ ለማጠየቅና ሰልፍ ለመውጣት አስባችኋል በሚል ተማሪዎችን ማሰር እና ከትምህርት ገበታቸው ላይ ማባረር ለረጅም አመታት ሲፈፀም የቆየ ነው፡፡ *"የኦሮሞ ህዝብ ሰልፍ ሊወጣ ነው ብላችኋል"* በሚል ተማሪዎችን በህዝባዊ አመፅ አስተባባሪነት በሚፈረጅ አሰቃቂ ድርጊት ከሚፈፀመው በላይ ኢ-ፍትሀዊ ወሳኔ ስለተላለፈባቸው ብሄራዊ የኦሮሞ ወጣቶች ንቅናቄ ይህን ድርጊት በጥብቅ ያወግዘዋል፡፡ የወያኔ መንግስት የኦሮሞ ተማሪዎችን በማሰር እና የኦሮሞን ህዝብ ከመኖሪያ አካባቢው በሚፈናቀል የፖለቲካ ችግሩን ለመፍታት ማጣሩ የህዝቡን የፀረ ባርነት ትግል መቀልበስ እንደማይችል እንገነዘባለን፡፡

የኦሮሞ ተማሪዎች በአንድ በኩል የፀረ ባርነት ትግሉን ለማቀናጀት አስባችኋል እየተባሉ እየተወነጀሉና እየታሰሩ የሚኙ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ባልፈፀሙት ድርጊት አሸባሪ ተብሎ በሚፈረጅ ትርጉም የሌለው ክስ ቀርቦባቸው የእስር ወሳኔ ከተሰጠባቸው መካከል፡-

1. ተማሪ ደቻሳ ዊርቱ፡- ከሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ከ 8 ዓመት፣
2. ተማሪ ኤቢሳ ራቱሳ፡- ከአምቦ ዩኒቨርሲቲ 8 ዓመት፣
3. ተማሪ አዳሙ ሽፈራው፡- ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 8 ዓመት፣
4. አቶ በርሲሳ ለሚ፡- የአዲስ አበባ ነዋሪ ሲሆን 4 ዓመት፣
5. መምህር ብርሃኑ እምሩ፡- የኮተቤ ኮሌጅ መምህር ሲሆን 4 ዓመት፣
6. ተማሪ ጌቱ ሳቃታ፡- ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 3 ዓመት፣
7. ተማሪ ሴና ሚረራ፡- ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ 3 ዓመት፣
8. ጋዜጠኛ አለሙ ተሾመ፡- የአዲስ አበባ ነዋሪ ሲሆን 3 ዓመት፣
9. ተማሪ ዲሪብሳ ዳምጤ፡- ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 3 ዓመት፣
10. ተማሪ ስለሺ ሶሪ፡- ከሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ 3 ዓመት፣
11. ተማሪ አብዲሳ ጉደታ፡- ከመዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ 3 ዓመት፣
12. ተማሪ ሜሬሳ ኃ/ኢየሱስ፡- ከአዲስ አበባ የግል ኮሌጅ 3 ዓመት፣
13. ተማሪ ደሜ ዘሪሁን፡- ከአዲስ አበባ የግል ኮሌጅ 3 ዓመት፣
14. ተማሪ አብዲ ደረጀ፡- ከወለጋ ዩኒቨርሲቲ 4 ዓመት፣
15. ተማሪ አለማየሁ ራጋሳ፡- ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ 3 ዓመት፣
16. ተማሪ ደረጀ ጌቱ፡- 3 ዓመት፣
17. ተማሪ ዳግም በቀለ፡- ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ 3 ዓመት፣
18. ተማሪ ጌታቸው አበራ፡- ከሻምቡ 3 ዓመት፣
19. ተማሪ ሻፊ ሰኢድ፡- ከጅማ ዩኒቨርሲቲ 3 ዓመት፣
20. ጅሬኛ ደሳለኝ፡- 3 ዓመት ከ3 ወር፣
21. አለማየሁ ረጋሳ፡- 3 ዓመት፣
22. ሻሼ ሰኢድ፡- 3 ዓመት፣
23. መምህር ለሚ፡- 4 ዓመት፣ እንዲሁም
24. አለሙ ተሾመ፡- 3 ዓመት እስራት ተፈርዶባቸዋል፡፡

ከላይ ስማቸው የተገለጹት የኦሮሞ ተማሪዎች ያለምንም ጥፋት ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ከትምህርት ገበታቸው በማዛዝ የታሰሩ ሲሆን ይህ መንግስት በኦሮሞ ተወላጆች ላይ እየወሰደ ያለው የጠላትነት ወሳኔ የተጨቋኙን ህዝብ ቁስል የበለጠ ያደማል እንጂ ትግሉ እንደሚቆም ማታወቅ አለበት፡፡

ብሄራዊ የኦሮሞ ወጣቶች ንቅናቄ የኢፌዴሪ መንግስት በኦሮሞ ላይ የሚፈፀመውን አረሜያዊ ድርጊት እንዲያቆም በጥብቅ ያሳስባል፡፡

ትግሉ ይቀጥላል! የባርነት አገዛዝ ይወድቃል!

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

ብሄራዊ የኦሮሞ ወጣቶች ንቅናቄ

ነሀሴ 2013 አዲስ አበባ